ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ — ረመዳን 12/1440 ሂ.

አውቃፍ ሚኒስትር — ሜይ 17/2019 ግ.


(1)

## የኩራት፣ የትእቢትና ከአላህ (ዐ.ወ.)ሃይማኖት የመከልከል ገጽታዎች

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{سَأَصْرِفُ عَنْ آيَاتِيَ الَّذِينَ يَتَكَبَّرُونَ فِي الأَرْضِ بِغَيْرِ الْحَقِّ وَإِنْ يَرَوْا كُلَّ آيَةٍ لا يُؤْمِنُوا بِهَا وَإِنْ يَرَوْا سَبِيلَ الرُّشْدِ لاَ يَتَّخِذُوهُ سَبِيلاً وَإِنْ يَرَوْا سَبِيلَ الْغَيِّ يَتَّخِذُوهُ سَبِيلاً ذَلِكَ بِأَنَّهُمْ كَذَّبُوا بِآيَاتِنَا وَكَانُوا عَنْهَا غَافِلِينَ}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (እነዚያን ያለአግባብ በምድር ላይ የሚኮሩትን ከአንቀጾቼ በእርግጥ አዞራቸዋለሁ፡፡ ተዓምርንም ሁሉ ቢያዩ በርሷ አያምኑም፡፡ ቅንንም መንገድ ቢያዩ መንገድ አድርገው አይዙትም፡፡ ግን የጥመትን መንገድ ቢያዩ መንገድ አድርገው ይይዙታል፡፡ ይህ እነርሱ በአንቀጾቻችን ስለአስተባበሉና ከእርሷም ዘንጊዎች ስለኾኑ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

በግለሰብም ሆነ በማህበረሰብ ደረጃ የኩራተኞች መጨረሻ በዚህች ዓለምም ሆነ በመጭው ዓለም እጅጉን አስከፊ ነው፡፡ የነዚያ ያመጡና በትእቢት የተወጠሩ ህዝቦችና መንደሮቻቸው ጥፋት በሰው ልጅ ሕይዎት የደነገገው የአላህ (ዐ.ወ.) ቋሚ ህግ ነው፡፡ ለአላህም ድንጋጌ ፈጽሞ መለወጥን እንድሁም መዛወርን አታገኝም፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

﴿فَأَمَّا عَادٌ فَاسْتَكْبَرُوا فِي الْأَرْضِ بِغَيْرِ الْحَقِّ وَقَالُوا مَنْ أَشَدُّ مِنَّا قُوَّةً أَوَلَمْ يَرَوْا أَنَّ اللَّهَ الَّذِي خَلَقَهُمْ هُوَ أَشَدُّ مِنْهُمْ قُوَّةً وَكَانُوا بِآيَاتِنَا يَجْحَدُونَ * فَأَرْسَلْنَا عَلَيْهِمْ رِيحًا صَرْصَرًا فِي أَيَّامٍ نَّحِسَاتٍ لِّنُذِيقَهُمْ عَذَابَ الْخِزْيِ فِي الْحَيَاةِ الدُّنْيَا وَلَعَذَابُ الْآخِرَةِ أَخْزَى وَهُمْ لَا يُنصَرُونَ ﴾

ትርጉሙም (ዓድም በምድር ላይ ያለ አግባብ ኮሩ፡፡ «ከእኛ ይበልጥ በኀይል ብርቱ ማን ነው?» አሉም፡፡ ያ የፈጠራቸው አላህ እርሱ በኀይል ከእነርሱ ይበልጥ የበረታ መኾኑን አያዩምን? በተዓምራታችንም ይክዱ ነበሩ፡፡ በቅርቢቱ ሕይወት የውርደትን ቅጣት ልናቀምሳቸውም በእነርሱ ላይ የሚንሻሻን ብርቱ ነፋስ መናጢዎች በኾኑ ቀናት ውስጥ ላክንባቸው፡፡ የመጨረሻይቱም (ዓለም) ስቃይ በጣም አዋራጅ ነው፡፡ እነርሱም አይረዱም፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

﴿وَكَأَيِّن مِّن قَرْيَةٍ عَتَتْ عَنْ أَمْرِ رَبِّهَا وَرُسُلِهِ فَحَاسَبْنَاهَا حِسَابًا شَدِيدًا وَعَذَّبْنَاهَا عَذَابًا نُّكْرًا* فَذَاقَتْ وَبَالَ أَمْرِهَا وَكَانَ عَاقِبَةُ أَمْرِهَا خُسْرًا﴾ .

ትርጉሙም (ከከተማም ከጌታዋ ትዕዛዝ ከመልክተኞቹም ያመጸች፣ ብርቱንም ቁጥጥር የተቆጣጠርናት፣ መጥፎንም ቅጣት የቀጣናት ብዙ ናት፡፡ የነገርዋንም ቅጣት ቀመሰች፡፡ የነገርዋም መጨረሻ ከሳራ ኾነ፡፡) ማለት ነው፡፡

ኩራት አላህ (ኢ.ወ.) ለመጀመሪያ ጊዜ የተወነጀለበት ኃጢአት ነው፡፡ ይህውም ታላቁ አላህ መላእኮች ለአደም እንዲሰግዱ ባዘዘ ጊዜ ሁሉም ሰገዱ ከኢብሊስ በስተቀር፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡፡

﴿وَإِذْ قُلْنَا لِلْمَلَائِكَةِ اسْجُدُوا لِآدَمَ فَسَجَدُوا إِلَّا إِبْلِيسَ أَبَى وَاسْتَكْبَرَ وَكَانَ مِنَ الْكَافِرِينَ﴾.

ትርጉሙም (ለመላእክትም «ለአደም ስገዱ» ባልን ጊዜ (አስታውስ) ፡፡ ሁሉም ወዲያውኑ ሰገዱ፤ ኢብሊስ (ዲያብሎስ) ብቻ ሲቀር እምቢ አለ፤ ኮራም ከከሓዲዎቹም ኾነ፡፡”) ማለት ነው፡፡

ኩራተኞች በዚህች ዓለም ይለዩባቸው በነበሩት አጻያፊ ገጽታዎች በመጭው ዓለምም እንደዚሁ ይለዩባቸዋል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ብሏል፡

{وَنَادَى أَصْحَابُ الأَعْرَافِ رِجَالاًيَعْرِفُونَهُم بِسِيمَاهُمْ قَالُوا مَا أَغْنَى عَنكُمْ جَمْعُكُمْ وَمَا كُنتُمْ تَسْتَكْبِرُونَ}

ትርጉሙም ( የአዕራፍም ሰዎች በምልክታቸው የሚያውቁዋቸውን (ታላላቅ) ሰዎች ይጣራሉ፡፡ «ስብስባችሁና በብዛታችሁ የምትኮሩ መኾናችሁም ከእናንተ ምንም አልጠቀማችሁ» ይሏቸዋል፡፡) ማለት ነው፡ ፡

በመሆኑም የእስልምና እምነት የኩራት መጨረሻው አስከፊ መሆኑን አስጠንቅቋል፡፡ ከአላህ እዝነት የሚያርቅ መንገድ መሆኑንም ጠቁሟል፡፡ ኩራተኞችም አሳማሚ ቅጣት እንደሚተብቃቸው ዝቷል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{إِنَّ الَّذِينَ كَذَّبُوا بِآيَاتِنَا وَاسْتَكْبَرُوا عَنْهَا لاَ تُفَتَّحُ لَهُمْ أَبْوَابُ السَّمَاءِ وَلاَ يَدْخُلُونَ الْجَنَّةَ حَتَّى يَلِجَ الْجَمَلُ فِي سَمِّ الْخِيَاطِ وَكَذَلِكَ نَجْزِي الْمُجْرِمِينَ}

ትርጉሙም ( እነዚያ አንቀጾቻችንን ያስተባበሉ ከእርሷም የኮሩ ለእነርሱ የሰማይ ደጃፎች አይከፈቱላቸውም፡፡ ግመል በመርፌ ቀዳዳ እስከሚገባም ድረስ ገነትን አይገቡም፡፡ እንደዚሁም አጋሪዎችን እንቀጣለን፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَيَوْمَ الْقِيَامَةِ تَرَى الَّذِينَ كَذَبُوا عَلَى اللَّهِ وُجُوهُهُم مُّسْوَدَّةٌ أَلَيْسَ فِي جَهَنَّمَ مَثْوًى لِّلْمُتَكَبِّرِينَ}

ትርጉሙም (በትንሣኤ ቀንም እነዚያን በአላህ ላይ የዋሹትን ፊቶቻቸው የጠቆሩ ኾነው ታያቸዋለህ፡፡ በገሀነም ውስጥ ለትዕቢተኞች መኖሪያ የለምን?) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (ገነትና እሳት ተከራከሩ፡ እሳት በኔ ውስጥ ኃያላንና ኩሩዎች አሉ አለች፡፡ ጀነትም በኔ ውስጥ ከሰዎች ደካሞቹና ምስኪኖቹ አሉ አለች፡፡ ከዚያም አላህ (ዐ.ወ.) ከነሱ መካከል በመዳኘት እንድህ አለ፡ (አንች ገነት እዝነቴ ነሽ ባንቺ ለፈለግሁት ምህረት አደርጋለሁ፡፡ አንች አሳት ደግሞ ቅጣቴ ነሽ ባንች የፈለግሁትን እቀጣለሁ፡፡ ሁለታችሁንም እኔ ልሞላችኋለሁ ቃል እገባለሁ፡፡) እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ (... የእሳት ሰዎች እነማን እንደሆኑ ልንገራችሁን? ገብጋባ ገንዘብ አካባችና ትእቢተኛ ሁሉ ናቸው)፡፡

ኩራት በበሽተኛ ልብ ውስጥ የሚሰፍን ባሕርይ መሆኑ ጥርጥር የለበትም፡ ፡ አንድ ሰው ኑሮው ዝቅተኛና ንብረቱም ቀላል ሆኖ እያለ ሲምበጠረር ይስተዋላል፡፡ ሌላው ደግሞ ባለሰፊ ጸጋና ይህች ዓለም ስፍታለት እያለ ራሳቸውን ዝቅ ከሚያደርጉና ከሚተናነሱት ሰዎች መካከል ይገኛል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (በልቡ ቅንጣትም ብትሆን ኩራት ያለችበት ሰው ጀነት አይገባም፡፡) ያን ጊዜ አንድ ሰው አንድ ሰው ልብሱ ጫማውም ያማረ እንድሆን ይፈልጋል ሲል ጠየቀ፡፡ እሳቸውም (አላህ (ሱ.ወ.) ውብ ነው ውበትንም ይወዳል፡፡ ኩራት ማለት መብትን መጋፋትና ሰዎችን ማንኳሰስ ነው፡፡) አሉ፡፡ ኩራት መንፈስን የሚሰብሩና ማህበረሰብን የሚያወድሙ አደገኛ ከሚባሉት የስነ ልቦናና የማህበራዊ በሽታዎች እንደኛው ነው፡፡ የኩራት ባለቤት በኩራቱ ሰዎችን ዝቅ አድርጎ በማየቱ ራሱን የሚያታልል ሰው ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{إِنْ فِي صُدُورِهِمْ إِلاَّ كِبْرٌ مَا هُمْ بِبَالِغِيهِ}.

ትርጉሙም(በልቦቻቸው ውስጥ እነርሱ ደራሾቹ ያልኾኑት ኩራት ብቻ እንጅ ምንም የለም፡፡) ማለት ነው፡፡

ኩራት በመንፈስ ውስጥ የሚሰፍን ባሕርይ ቢሆንም በስርኣትና ከሰዎች ጋር በሚደረግ እንቅስቃሴ ጎልተው የሚታዩ በርካታ ገጽታዎች አሉት፡፡ ከነሱም በቅድሚያ የሚጠቀሱት ትእቢቱ በኃጢያት ሥራ የሚገፋፋው መሆኑና ለእውነት አለመገዛቱ የሚሉት ናቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ሳል፡

{....وَإِذَا قِيلَ لَهُ اتَّقِ اللَّهَ أَخَذَتْهُ الْعِزَّةُ بِالْإِثْمِ}

ትርጉሙም (ለእርሱ «አላህን ፍራ» በተባለም ጊዜ፤ ትዕቢቱ በኃጢኣት (ሥራ) ላይ ትገፈፋዋለች፡") ማለት ነው፡፡

ኩራተኛ ሰው አስከፊው መታለሉና አጸያፊ ኩራቱ እውነትን እንዳይቀበል የሚያደርጉት ሲሆን ወደእውነት ሲጠሩት መታለልንና መንበጣረረን ይጨምረዋል፡፡ በመሆኑም ራሱን ወደጥፋት ይከታል፡፡ በገሀነምም ይቀጣል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{ فَحَسْبُهُ جَهَنَّمُ وَلَبِئْسَ الْمِهَادُ}

ትርጉሙም(ገሀነምም በቂው ናት፤ (እርሷም) በእርግጥ የከፋች ምንጣፍ ናት፡፡") ማለት ነው፡፡

ከሰዎች መካከል በነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ትእዛዝም ሳይቀር የሚተበትና የትእቢቱንና የሞገዱን ዋጋ የሚያገኝ ሰው አለ፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ኢያስ ኢብን ሰለማህ ኢብን ኢል አክወዕ አባታቸውን ጠቅሰው የሚከተለውን እውርተዋል፡ ‹አንድ ሰውዬ ከነብያችን አጠገብ በግራ እጁ መመገብ ጀመረ እሳቸውም (በቅኝ ብላ) አሉት፡፡ እሱም አልችልም አለ፡፡ እሳቸውም (አትቻል) አሉት፡፡ ያ ሰው ኩራቱ እንጅ በቀኙ ከሙብላት የሚያግደው ነገር አልነበረም፡፡ ኢብን ሰለማ እንድህ አሉ፡ ያ ሰውዬ እጁን ወደአፉ ማድረስ አልቻለም፡፡›

ሌላው የኩራት ገጽታ ደግሞ በኩራት ፊትን ከሰዎች ማዞር የሚለው ነው፡፡አላህ (ሱ.ወ.) በሉቅማግን ልሳን እንድህ ይላል፡

{ وَلا تُصَعِّرْ خَدَّكَ لِلنَّاسِوَلا تَمْشِ فِي الأَرْضِ مَرَحًا إِنَّ اللَّهَ لا يُحِبُّ كُلَّ مُخْتالٍ فَخُورٍ}

ትርጉሙም («ጉንጭህንም (በኩራት) ከሰዎች አታዙር፡፡ በምድርም ላይ ተንበጥርረህ አትሂድ፡፡ አላህ ተንበጥራሪን ጉረኛን ሁሉ አይወድምና፡፡) ማለት ነው፡፡

በአረማመድ መንበጣረር ሌላው የኩራት ገጽታ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَلاَ تَمْشِ فِي الأَرْضِ مَرَحًا إِنَّكَ لَن تَخْرِقَ الأَرْضَ وَلَن تَبْلُغَ الْجِبَالَ طُولاً كُل ذَلِكَ كَانَ سَيِّئُهُ عِنْدَ رَبِّكَ مَكْرُوهًا}

ትርጉሙም(በምድርም ላይ የተንበጣረርክ ሆነህ፤ አትሂድ፡፡ አንተ ፈጽሞ ምድርን አትሰረጉድምና በርዝመትም ፈጽሞ ጋራዎችን አትደርስምና፡፡) ማለት ነው፡፡

በእርስትና አላህ በቸረው ጸጋም መፎከር ከኩራት ገጽታ ይመደባል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ከናንተ በፊት ከነበሩት ህዝቦች አንድ ሰው አንድ ቀን ውብ ሸማና ሸርጡን ለብሶ በኩራት በሰዎች መካከል ወጣ፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) መሬትን እንድትውጠው አዘዛት እነሆ እስከ ትንሳኤም ቀን ድረስ እንደሰጠመ ይኖራል፡፡) ትእቢት በልብስ እንደሚሆን ሁሉ በቤት ምንጣፍ፣ በመኪናና የተለየ ቤትን በመግዛትም ሊከሰት ይችላል፡፡ ከድሆችና ከደካሞች ጋር መቀመጥን መናቅ ሌላው የትእቢት ገጽታ ነው፡፡ አጋሪዎች ከድሃ የነብያችን ባልደረቦች ከሰልማን፣ ከሱሃይብና ከቢላል ጋር መቀመጥን ይንቁ ነበር፡፡ ከዚያም አልፎ ለአላህ መልክተኛ አነዚህን አባር በኛ ላይ እጠዳፈሩ ነውና በማለታቸው ታላቁ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ የምትለዋን አንቀጽ አወረደ፡

{ وَلاَ تَطْرُدِ الَّذِينَ يَدْعُونَ رَبَّهُمْ بِالْغَدَاةِ وَالْعَشِيِّ يُرِيدُونَ وَجْهَهُ}

ትርጉሙም (እነዚያን ጌታቸውን ፊቱን (ውዴታውን) የሚሹ ኾነው በጧትና በማታ የሚጠሩትን አታባርር፡፡) ማለት ነው፡፡

በድግስ ጊዜ ባለጸጋዎችን መጥራትና ድሆችን ንቆ መተው ሌላው የኩራት ገጽታ ነው፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ ሁረይራህ እንድህ ብለዋል፡ ‹ከመግብ እጅግ መጥፎው ሃብታሞች የሚጠሩበትና ድሃዎች የሚተውበት ድግስ ምግብ ነው፡፡› ከኩራት ገጽታዎች ሌላው ደግሞ በደረጃ ከሱ በታች የሆነን ሰው ንቆ ሰላምታ አለማለት ወይም እሱን አለመጨበጥ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በህጻናት አጠገብ ሲያልፉ ሰላምታ ያቀርቡላቸው ነበር፡፡ በክርክር መፋጠጥና በሱም መሰመርን መልቀቅ የኩራት ሌላው ገጽታ ነው፡፡ መቆራረጥና ብልሹነትን ስለሚያስከትል አንድ ሰው ወንድሙን ከሦስት ቀን በላይ እንዳያኮርፍ ተከልክሏል፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ወንድሙን ከሦስት ቀን በላይ ያኮረፈ አላህ በቸርነቱ ምህረት ካለደረገለት በስተቀር እሱ እሳት ይገባል፡፡) እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ (አንድ ሙስሊም ሙስሊም ወንድሙን ከሦስት ቀናት በላይ ሊያኮርፈው አይፈቀድለትም፡፡ አነሱ ሲገናኙ አንዱ ለሌላው ጀርባውን ይሰጣል፡፡ ከነሱም በላጩ ያ በሰላምታ የቀደመው ነው፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (አራት ነገሮች በሱ ያሉበት ሰው ሙሉ መናፍቅ ነው፡፡ ከነሱ አንዱ ያለበት ደግም እሱን እስከሚያሰውገድ ድረስ ከመናፍቅነት ገጽታዎች አንዱ አለበት፡፡ -እነሱም- እምነት ሲጣልበት ይከዳል፣ ሲያወራም ይዋሻል፣ ቃል ሲገባም ቃሉን ያፈርሳል፣ ሲከራከርም መስመር ይለቃል፡፡) አጋሪዎች እስልምናን እንዳይቀበሉ የከለከላቸውና (لا إِلَٰهَ إلا الله) ከማለትም ያገዳቸው ኩራትና ትእቢት ብቻ ነበር፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{إِنَّهُمْ كَانُوا إِذَا قِيلَ لَهُمْ لَا إِلَٰهَ إِلَّا اللَّهُ يَسْتَكْبِرُونَ}

ትርጉሙም (እነርሱ ከአላህ ሌላ አምላክ የለም በተባሉ ጊዜ ይኮሩ ነበሩ፡፡ ) ማለት ነው፡፡

አይሁዳዎችም በነብይነታቸው እውነተኛነት እርግጠኞች ሆነው ሳል ነብያችንን ከመከተል የከለከላቸው ትእቢት ብቻ ነበር፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{الَّذِينَ آتَيْنَاهُمُ الْكِتَابَ يَعْرِفُونَهُ كَمَا يَعْرِفُونَ أَبْنَاءَهُمْ وَإِنَّ فَرِيقًا مِنْهُمْ لَيَكْتُمُونَ الْحَقَّ وَهُمْ يَعْلَمُونَ}

ትርጉሙም(እነዚያ መጽሐፍን የሰጠናቸው ወንዶች ልጆቻቸውን እንደሚያውቁ (ሙሐመድን) ያውቁታል፡፡ ከነሱም የተለዩ ክፍሎች እነርሱ የሚያወቁ ሲኾኑ እውነቱን በእርግጥ ይደብቃሉ፡፡) ማለት ነው፡፡

የእስራኢል ልጆች ነብዮቻቸውን ውሸታም እንድሉና ከፊሎችንም እንድገድሉ ያደረጋቸው ያው ትእቢት ነው፡፡ አላህ(ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{فَكُلَّمَا جَاءَكُمْ رَسُولٌ بِمَا لاَ تَهْوَى أَنفُسُكُمُ اسْتَكْبَرْتُمْ فَفَرِيقاً كَذَّبْتُمْ وَفَرِيقاً تَقْتُلُونَ}.

ትርጉሙም ( ነፍሶቻችሁ በማትወደው ነገር መልክተኛ በመጣላችሁ ቁጥር (ከመከተል) ትኮራላችሁን? ከፊሉን አስተባበላችሁ፤ ከፊሉንም ትገድላላችሁ፡፡) ማለት ነው፡፡

የላፉት ህዝቦት ነብዮቻቸውን ውሸታም ናችሁ እንድሉ ያደረው ራሱ ትእቢት ነው፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) በነብዩ ኑሕ ልሳን እንድህ ይላል፡

{وَإِنِّي كُلَّمَا دَعَوْتُهُمْ لِتَغْفِرَ لَهُمْ جَعَلُوا أَصَابِعَهُمْ فِي آذَانِهِمْ وَاسْتَغْشَوْا ثِيَابَهُمْ وَأَصَرُّوا وَاسْتَكْبَرُوا اسْتِكْبَارًا}

ትርጉሙም(«እኔም ለእነርሱ ትምር ዘንድ (ወደ እምነት) በጠራኋቸው ቁጥር ጣቶቻቸውን በጆሮዎቻቸው ውስጥ አደረጉ፡፡ ልብሶቻቸውንም ተከናነቡ፡፡ (በመጥፎ ሥራቸው ላይ) ዘወተሩም፡፡ (ያለ ልክ) መኩራትንም ኮሩ፡፡ ) ማለት ነው፡፡

እንድሁም ስለነብዩ ሁድ ሰዎች ሲያብራራ እንድህ ይላል፡

{فَأَمَّا عَادٌ فَاسْتَكْبَرُوا فِي الْأَرْضِ بِغَيْرِ الْحَقِّ وَقَالُوا مَنْ أَشَدُّ مِنَّا قُوَّةً}

ትርጉሙም(ዓድም በምድር ላይ ያለ አግባብ ኮሩ፡፡ «ከእኛ ይበልጥ በኀይል ብርቱ ማን ነው?» አሉም፡፡) ማለት ነው፡፡ ስለሷሊሕ ሰዎችም እንድህ ብሏል፡

{قَالَ الْمَلأُ الَّذِينَ اسْتَكْبَرُواْ مِن قَوْمِهِ لِلَّذِينَ اسْتُضْعِفُواْ لِمَنْ آمَنَ مِنْهُمْ أَتَعْلَمُونَ أَنَّ صَالِحًا مُّرْسَلٌ مِّن رَّبِّهِ قَالُواْ إِنَّا بِمَا أُرْسِلَ بِهِ مُؤْمِنُونَ * قَالَ الَّذِينَ اسْتَكْبَرُواْ إِنَّا بِالَّذِيَ آمَنتُمْ بِهِ كَافِرُونَ}

ትርጉሙም(ከወገኖቹ እነዚያ የኮሩት መሪዎች ለእነዚያ ለተሸነፉት ከነሱ ላመኑት፡- «ሷሊህ ከጌታው መላኩን ታውቃላችሁን» አሏቸው፡፡ «(አዎን)፡- እኛ እርሱ በተላከበት ነገር አማኞች ነን» አሉ፡፡ እነዚያ የኮሩት፡ - «እኛ በዚያ እናንተ በርሱ ባመናችሁበት ከሓዲዎች ነን» አሉ፡፡) ማለት ነው፡፡ ስለሹዓይብ ህዝቦችም እንድህ ብሏል፡

(قَالَ الْمَلأُ الَّذِينَ اسْتَكْبَرُواْ مِن قَوْمِهِ لَنُخْرِجَنَّكَ يَا شُعَيْبُ وَالَّذِينَ آمَنُواْ مَعَكَ مِن قَرْيَتِنَا أَوْ لَتَعُودُنَّ فِي مِلَّتِنَا)

ትርጉሙም(ሕዝቦቹ እነዚያ የኮሩት መሪዎች፡- «ሹዓይብ ሆይ! አንተንና እነዚያን ከአንተጋር ያመኑትን ከከተማችን በእርግጥ እናስወጣችኋለን፡፡ ወይም ወደ ሃይማኖታችን መመለስ አለባችሁ አሉ፡፡) ማለት ነው፡፡

በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ በአላህ ትእዛዝ ላይ የተበተ ህዝብ ሁሉ መጨረሻ ጥፋት ነበር፡፡ ምን ይከፋ መጨረሻ፡፡ በዚህ አስቸጋሪ በሽታ የተለከፈ ሰው ከህመሙ ለመዳን ለልቡ ፈውስ ማፈላለግ ይኖርበታል፡፡ ይህም ፈውስ እንዲሳካ የራሱን ደረጃ ማወቅና ከአፈር ከዚያም ከፍተወት ጠብታ ከዚያም ከረጋ ደምና ከስጋ የተፈጠረ መሆኑን አለመርሳት ይኖርበታል፡፡ ማንኛውም ትእቢተኛ ሰው በመጭው ዓለም በነበረበት ተጻራሪ የሚቀጣ መሆኑን ማወቅ አለበት፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ

ብለዋል፡ (ትእቢተኞች በትንሳኤ ቀን በሁሉም አቅጣጫ ውርደት ያካበባቸውና የሰው ቅርጽ ያለው ቅንጣት ሆነው ይነሳሉ...) አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{تِلْكَ الدَّارُ الْآخِرَةُ نَجْعَلُهَا لِلَّذِينَ لَا يُرِيدُونَ عُلُوًّا فِي الْأَرْضِ وَلَا فَسَادًا وَالْعَاقِبَةُ لِلْمُتَّقِينَ}.

ትርጉሙም (ይህች የመጨረሻይቱ አገር ለእነዚያ በምድር ውስጥ ኩራትንና ማመፅን ለማይፈልጉት እናደርጋታለን፡፡ ምስጉኒቱም መጨረሻ ለጥንቁቆቹ ናት፡፡) ማለት ነው፡፡

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

***

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትና በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

ከአላህ (ዐ.ወ.) መንገድ መከልከል ገጽታዎች አንዱ ደግሞ የአንድ ሰው ቃላት የተግባራቱ ተጻራሪ መሆናቸው ነው፡፡ ከዋና አላማዎችና መሰረታዊ ነገሮች ይልቅ ለቅርጽና ለውጫዊ ገጽታ ከፍተኛ ትኩረትና ሙሉ ቅድሚያ የሚሰጡ ሰዎች በትክክለኛው የአላህ መንገድ ላይ አይደሉም፡፡ ምክኒያቱም በርካታ ለውጫዊ ገጽታ ቅድሚያ የሚሰጡ ወገኖች ባሕርያቸውና ስርአታቸው ከእስልምና መመሪያዎች ጋር የሚጻረር በመሆኑ ሰዎች ከሃይማኖቱ እንድደነብሩ ያደርጋልና ነው፡፡ በዚህም

ከአላህ መንገድ የተከላከሉና ሃይማኖቱንም የሚጎዱ ይሆናሉ፡፡ እነሱም ነብያችን (ከናንተ መካከል ከሃይማኖት የሚያስደብሩ አሉ፡፡) ከአሏቸው ወገኖች ይካተታሉ፡፡

አንድ ሰው ውጫዊ ገጽታው ሃይማኖተኛ መስሎ ከሰው ጋር በሚዋዋልበት ወቅት በአስከፊ ውሸት፣ ክዳት፣ ክህደትና የሰዎችን ገንዘብ በከንቱ መብላት ሲዘፈቅ የሚታይ ከሆነ ነገሩ እጅግ አደገኛ ይሆናል፡፡ ይልቁንም ይህ ሰው ከመናፍቃን ተርታ ይመደባል፡፡ ይህም በአላህ ሃማኖት የሚነግዱት አማፂያን አሸባሪ ቡድኖች ባሕርይ ነው፡፡ እንዚህ ቡድኖች ሽብርን እያስፋፉና እየደገፉ ሳለ ማንኛውንም መንገድ በመከተልና ሁሉንም መዳረሻ የጠፈቀደ በማድረግ በሀገራት በትረ ስልጣኑን ለመጨበጥ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ ይስተዋላሉ፡፡

እንድሁም ሃይማኖትን በአምልኮትና ለሱም ጥረት በማድረግ ብቻ የሚወስኑ ሃይማኖቱን በተሳሳተ መልኩ የተገነዘቡ ወገኖች በሰዎች ላይ መሳሪያ አንግበው በመነሳታቸው ከአላህ መንገድ ይከለክላሉ፡፡ ኸዋሪጅ በመባል የሚታወቁት ቡድኖች በስግደታቸውና በጾማቸው ተወዳዳሪ የሌላቸው ሆነው ሳለ በደም ማፍሰስ ወንጀል እንዳይገቡ የሚግዳቸው በቂ የሃይማኖት ህግ እውቀት ባለማካበታቸው በሰዎች ላይ መሳሪያ አንግበው ወጥተው ያልሆነ ውጤት ላይ አድርሷቸዋል፡፡ የእስልምና እምነት የእዝነት ሃይማኖት ነው፡፡ ከእዝነት የሚያርቅ ነገር ሁሉ ከእስልምናም ያርቃል፡፡ የማንኛውም ነገር መመዘኛ ትክክለኛ ስርአትና ተግባር እንጂ ቃል ብቻ አይደለም፡፡

ጌታችን ሆይ እውነተኛ እውነትን አሳውቀን መከተሉንም አሳካልን፡፡ ግልጽ ከንቱንም አሳውቀን ከሱ መራቅንም አሳካልን፡፡ አሜን፡፡